# መንፈሳዊ ኩራት ወሰደን ወደ ትዕቢት

ከኤርምያስ ሶፎንያስ

ጊዜና ማስተዋል፣ የልብ መነሳሳት፣ የእጆች መጻፍ፣ የንግግር ችሎታ፣ ጠቃሚ ሀሳብ ማፍለቅ ወዘተ የሚሰጡት ከላይ ከሰማይ እንደሆነ፤ ከውሸት ወደ እውነት፣ ከትዕቢት ወደ ትኅትና፣ ከራስ ወዳድነት መገንን ወደ ማሰብ፣ ወደፍቅረ ቢጽ መመለስ የሚችለው እግዚአብሔር ማስተዋሉን ሲሰጥ መሆኑን ለሁላችንም ግልጽ ነው። ከእናቱ ማኅፀን ወደዚህች ምድር የመጣ የሰው ልጅ ልዑል እግዚአብሔር አዕምሮውን ብሩህ ካላደረገለት ጥበብ መንፈሳዊውንና ጥበብ ሥጋዊን ለመረዳት የራሱ የሆነ ችሎታ ከየት? እንዴት? ለማግኘት ይችላል። ለነፍስና ለሥጋ የሚጠቅሙ ስጦታዎች ሁሉ ከአምላክ ይገኛሉ። ከዚህ በተለየ ሁኔታ ማለትም ሰው በአቅሙ፣ በብርታቱና በችሎታው ከአምላክ ያልተሰጠውን ለማግኘት ቢችል ኖሮ፤ ሁላችንም ለመበልጸግ ስንፈልግ መበልጸግ፣ ጤንነት ለማግኘት ስናስብ ደዌአችንን አስወግደን ፍጹም ጤነኞች ለመሆን እንችል ነበር። ደስታንም ለማግኘት ስናስብ ፍፁም ደስተኞች እንሆን ነበር። ግን አንችልም።

ዋናው ቁምነገር ከላይ ከሰማይ በእኛ ሕይወት የሚያዝ አምላክ መኖሩን መረዳቱ ላይ ነው። ልዑል አምላክም በእኛ የሚደሰተው፤ ምሕረቱንና ቸርነቱን ተረድተን የስጦታዎች መገኛ እርሱ መሆኑን ስናውቅ ላት ነው። እግዚአብሔር "ጠቢብ በጥበቡ አይመካ፣ ኃያልም በኃይሉ አይመካ፣ ባለጠጋም በብልጥግናው አይመካ፤ ነገር ግን የሚመካው ምሕረትንና ፍርድን፣ ጽድቅንም በምድር ላይ የማድርግ እኔ እግዚአብሔር መሆኔን በማወቁና በማስተዋሉ በዚህ ይመካ፤ ደስ የሚያሰኙኝ እነዚህ ናቸውና።" ይለናል።(ኤር. ፱÷፳፫ - ፳፬)

መንፈሳዊ ኩራት ምንድን ነው? በብዙ መንፈሳዊ ሥፍራዎች በኮሚቴዎች ተዋቅረው የአገልግሎታቸውንና የሥራ ውጤታቸውን በማስመልከት በሚያቀርቡት ሪፖርት ላይ፤ "መንፈሳዊ ኩራት" ተሰምቶናል፣ በአገልግሎታችሁ መንፈሳዊ ኩራት ሊሰማችሁ ይገባል ወዘተ. የሚሉ ንግግሮችን እናዳምጣለን። በመሠረቱ ኩራት የሥጋ ጠባይ የትዕቢት ልጅ መሆኑ መዘንጋት አይኖርበትም።

በመንፈስ የተጀመረ አገልግሎት እግዚአብሔርን በማመስገን ሊፈጸም ይገባዋል እንጂ፤ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ተሰርቶ ታቦቱ ወደመንበር ሲገባ፣ የሰበካ ጉባኤ የልማት ሪፖርት ሲቀርብ፣ ዓመታዊ በዓልን ለማክበር የተዘጋጀው ኮሚቴ ሥራውን ሲያጠናቅቅ፤ መንፈሳዊ ኩራት ተሰምቶናል፣ በዚህ ተሳትፎአችሁ መንፈሳዊ ኩራት ሊሰማችሁ ይገባል፤ በማለት የሚደመጥ ንግግር ከቅዱስ መጽሐፍ አንፃር ስህተት መሆኑን መረዳት አለብን።

"ደግሞም እግዚአብሔር እንዲህ አለ የጽዮን ቆነጃጅት ኮርተዋልና፤ አንገታቸውንም እያሰገጉ በዓይናቸውም እያጣቀሱ፣ ፈንጠርም እያሉ፣ በእግራቸውም እያቃጨሉ ይሄዳሉና። ስለዚህ ጌታ የጽዮንን ቆነጃጅት አናት በቡሀነት ይመታል።" ይላል (ኢሳ. ፫÷፲፮ - ፲፯) ልዑል እግዚአብሔር በኩራት ምክንያት የጽዮን ቆነጃጅት እስኪዋረዱና ትኅትናን ገንዘብ እስኪያደርጉ ድረስ በቡሀነት ቀጥቶአቸዋል "እስመ በትኅትና ረከበ ልዕልና" ተብሏል እንጂ መንፈሳዊ ሥራ በመሥራታችሁ መንፈሳዊ ኩራት ይሰማችሁ አልተባለም። የዲያብሎስ እዳም ኩራት መሆኑን ልንዘነጋው አይገባም።

የምድያም ሰዎች በእስራኤል ላይ መከራ በጸኑባቸው ጊዜ፤ ልዑል እግዚአብሔር ወደ እስራኤላውያን ተመለከተ፣ ከወንድሞቻቸው መካከልም ጌዴዎንን አስነሳላቸው። ጌዴዎንም የአምላኩን አስተማማኝ ክንድ በልዩ ልዩ ምልክቶች ከተረዳ በኋላ፤ ብዙ ሕዝብ አስከትሎ ምድያማውያንን ይከራከር ዘንድ ጉዞ ጀመረ። እግዚአብሔር ግን በሕዝቡ ብዛት አልተደሰተም ነበር። ጌዴዎንን በቃሉ አነጋገረው።

በመ. መሳ. ፯÷፪ - ፯ "...ከአንተ ጋር ያለው ሕዝብ በዝቶአል። ስለዚህ እስራኤል እጄ አዳነኝ ብሎ እንዳይታበይ እኔ ምድያምን በእጃቸው አሳልፌ አልሰጥም" እንዳለው ይናገራል። እንግዲህ የእግዚአብሔር መልእክት በራስ ጉልበትና ችሎታ መመካት እንዳይገባ፣ ከመልካም ውጤት ለመድረስና ድል ለማድረግ የሚቻለው በእግዚአብሔር ኃይል እንደሆነ ለማስተማር ነው።ከዚህ ታሪክ እንደምንረዳው በቁጥር ሦስት መቶ የሆኑ የእሥራኤል ሰዎች፤ በመቶ ሺህ ከሚቆጠሩ የምድያም ሰዎች ጋር ተዋግተው አስደናቂ ድልን በተጎናጸፉ ጊዜ፤ ጌዴዎን በድሉ ምክንያት የመንፈስ ኩራት ተሰማው የሚል ጽሑፍ ከታሪኩ አይነበብም። ይልቁንም የእስራኤል ሰዎች ጌዴዎንን "ከምድያም እጅ አድነኸናልና፤ አንተ፣ ልጅህም፣ የልጅ ልጅህም ደግሞ ግዙን አሉት። ጌዴዎንም እኔ አልገዛችሁም፣ ልጄም አይገዛችሁም፤ እግዚአብሔር ይገዛችኋል አላቸው።" ይላል (መ. መሳ. ፰÷፳፫ - ፳፫)

እንግዲህ የመንፈስ ኩራት የሚገባ ቢሆን ጌዴዎን በኮራ ነበር። ሁሉንም ሥራ ለእግዚአብሔር በመስጠት፣ በትኅትና ራሱን በሕዝቡና በአምላኩ ፊት አዋረደ። እንግዲህ መንፈሳውያን ሁሉ አርአያ ያደርጉት ዘንድ የሚገባው፤ የጌዴዎንን ከልብ የመነጨ ግሩም ትኅትና ነው። ልባችን በእውነትና በትኅትና የተሞላ ከሆነ፤ ከጌዴዎን ታሪክ አንፃር ሕይወታችን ሲፈተሽ መንፈሳዊ ኩራት በሚለው አስተሳሰባችን ከአምላካችን መራቃችንን ቅዱሳት መጻሕፍት ያረጋግጡልናል።

እስራኤል ሁሉ ተሰብስበው ጌዴዎን በላያቸው እንዲሰለጥን እንደፈቀዱለት ከዚህ በላይ ከተገለጠው ታሪክ አንብበናል። የጌዴዎን ምላሽም በግልጥ ተቀምጦአል። ቅድሚያ ለፈጣሪው ሰጥቶአል። እግዚአብሔር በእርሱ በኩል ድል መስጠቱ እውነት ቢሆንም፤ መሪነትን እንኳ ይገባኛል ብሎ አልተቀበለም።

አብዛኛውን ጊዜ በመንፈሳውያን መካከል የሚከሰተው የጠብና ክርክር መነሻም፤ እኔ ከማን አንሳለሁ የሚል ኩራት በመሆኑ። እኔ እበልጥ፣ እኔ እበልጥ በሚል ፉክክር፤ በሚፈጠሩ ቅሬታዎች በሥራችን ሌሎች ከሚማሩና ከሚጠቀሙ ይልቅ በመንቀፍ እንዲጎዱበትና እንዲሰናከሉበት እናደርጋቸዋለን። ይህ ደግሞ የሥራ ፍሬያችንን ዋጋ ቢስ ያደርገዋል።

ስለመልካም ሥራው ሰዎች ከፍ ያደረጉት ጌዴዎን፤ ውዳሴ ከንቱን በመናቅ ክብር ለሚገባው ፈጣሪ ክብርን ሰጠ እንጂ፤ ክብርን እንደ እንጀራ ተርቦ፣ እንደውሃም ተጠምቶ፣ እንደሸማም ሊጎናጸፉት ክብርት ሰውነቱን አልጋበዛትም። ዛሬ ስለፈጸምነው መንፈሳዊ ተግባራት ብዙ በማውራት፤ ሌሎች እንዲያደንቁን ሰውነታችንን ያስለመድናት፣ መንፈሳዊ ኩራት እያልን የተመጻደቅን፣ ከፍ ብለንም ሌሎችን የናቅን ባዶነታችንን ልንረዳ ይገባናል።

በመሠረቱ በበጎ ሥራና በተሰጠን ጸጋ ሌሎች ሊያመሰግኑንና ሊያደንቁን እንደሚችሉ ይታወቃል። ነገር ግን እኛ ምስጋና የሚገባው ለፈጣሪ መሆኑን በመረዳት፣ ጌዴዎንን አብነት አድርገን፣ ክብር ለሚገባው ፈጣሪ ክብር ይሰጠው ዘንድ፤ ሰዎች እኛን ሳይሆን አምላክን እንዲያውቁ እርሱን እንዲያመሰግኑና እንዲያመልኩ ማድረግ ይጠበቅብናል።

ለመሆኑ በሎዶቅያ የነበረው ኤጲስ ቆጶስ ስለምን ተግሳፅ ደረሰበት። በኩራቱ መሆኑን አልተረዳንም? "... ሀብታም ነኝና ባለጠጋ ሆኜአለሁ፣ አንድም ስንኳ

ወደ ገጽ ፳፫ ዞሯል

አያስፈልገኝም የምትል ስለሆንክ፤ ጎስቋላና ምስኪንም፣ ድሀም፣ ዕውርም፣ የተራቆትህም መሆንህን ስለማታውቅ፤ ባለጠጋ እንድትሆን፣ በእሳት የነጠረውን ወርቅ ተጎናጽፈህም እራቁትነትህ ኃፍረት እንዳይገለጥ፣ ነጭ ልብስን እንድታይም ዓይኖችህን የምትኳለውን ኩል ከእኔ ትገዛ ዘንድ እመክርሀለሁ...።" (ራእይ ፫÷፲፯-፲፰) ኤጲስ ቆጶሱ መልካም አገልግሎት እንደነበረው ቢታወቅም ነገር ግን በአገልግሎቱ ብቻ "መንፈሳዊ ኩራት" በማለት እንዲቀጥል ፈቃደ አምላክ አይደለምና ጉድለቱን እንዲያርም እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ይመክረዋል። እኛም ታውረንና በመንፈስ ድህነት ተሸመድምደን እያለን፤ ጥቂት ሥራዎቻችንን እንደተራራ ለሌለች ገዝፎ እንዲታይ በማድረግ ብንኮራ፣ በመንፈስ እውርነት ተሸፍነን፣ ነፍሳችን ከጸጋ እግዚአብሔር ተራቁታ ሳለ "የመንፈስ ኩራት" ብንል፤ እንደ ሎዶቅያው ኤጲስ ቆጶስ ወቀሳ ይደርስብናል "የተጻፈው ሁሉ ለእኛም ትግሳጽና ምክር እንዲሆን ከዘመናችን ደርሷልና" (፪ኛ ጢሞ. ፲፮ - ፲፯)

ክርስትና የመንፈስ መዋረድና ትኅትና እንጂ ኩራት አይደለም። በጾምና ጸሎት፣ አሥራትና በኩራት ወዘተ የኮሩ ሲወቅሱ እንደነበር እናስ ተውላለን። "...ፈሪሳዊው ቆሞ በልቡ ይህን ሲጸልይ፤ እግዚአብሔር ሆይ እንደ ሌላ ሰው ሁሉ ቀማኞችና ዓመፀኞች፣ አመንዝሮችም፣ ወይም እንደ ዚህ ቀራጭ ስላልሆንኩ አመሰግንሃ ለሁ፤ በየሳምንቱ ሁለት ጊዜ እጦማለሁ፣ ከማገኘውም ሁሉ አሥራት አወጣለሁ አለ። ቀራጩ ግን አምላክ ሆይ እኔን ኃጢአተኛውን ማረኝ እያለ ደረቱን ይደቃ ነበር። እላችኋለሁ ከዚያ ይልቅ ይህ ጻድቅ ሆኖ ወደ ቤቱ ተመለሰ" ይላል። (ሉቃ. ፲፰÷፲፩ - ፲፬) በሉቃስ ወንጌል ፲፯÷፯ - ፲ እንደተገለፀውም ከእግዚአብሔር በተሰጠን እውቀት፣ ሀብት፣ ጉልበትና ጊዜ ልንሠራ የታዘዝነው በጎ ምግባር በፈጸምን ጊዜ እንኳ፤ ምሥጋናንና ውዳሴ ከንቱን እንዳንሻ ኩራት ተሰምቶን በንግግራችንም ሆነ በተግባራችን እንዳንገልጸው፤ "የማንጠቅም ባሪያዎች ነን ልናደርገው የሚገባንን አድርገናል።" በሉ ብሎ አምላካችን መድኃኒታች ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀመዛሙርቱን እንደመከራቸው እኛንም ይመክርናል።

ሌሎች በእኛ ላይ ያለውን የአምላክ ጸጋ አክብረው ስላከበሩን ጠባያችን ተለውጦ፤ ለስማችን፣ ለክብራችንና ለውዳሴ ከንቱ የተጋለጥን፤ የምንንዝበት አቅጣጫ የተሳሳተ በመሆኑ ራሳችንን ልንመረምር ይገባል። "በሃይማኖት ብትኖሩ ራሳችሁን መርምሩ" ተብሏልና (፪ኛ. ቆሮ ፲፫÷፭)

"ስሙ፣ አድምጡ እግዘአብሔር ተናግሮአልና አትታበዩ፤ ሳትጨልም፣ እግራችሁም በጨለመችው ተራራ ላይ ሳትሰናከል፣ በተስፋ የምትጠባበቁትን ብርሃን ለሞት ጥላና ለድቅድቅ ጨለማ ሳይለውጠው ለአምላካችን ለእግዘአብሔር ክብርን ስጡ። ይህን ባትሰሙ ነፍሴ ስለ ትዕቢታችሁ በስውር ታለቅሳለች።" ይላል (ኤር. ፲፫÷፲፭ - ፲፯)

በአገልግሎት ላይ የተሰማራን ሰዎች ትልቅ ተፅዕኖ የሚያሳድርብን የጠላታችን የዲያብሎስ ፈተና ነው። አንድ ሰው መልካም ሲሰራ ማየት ለዲያቢሎስ ውጋቱ ነው ዝም ብሎ ማየት አይፈልግም። እግዘአብሔር አምላክ በእኛ አድሮ ያሠራንን ሥራ እኛ እንደሠራን አድርገን እንድንመለከት በውዳሴ ከንቱ ለመጣል በሰዎች አድሮ ሲክበን እንመለከታለን።

ባላጋራችን እኛን ከቤተ እግዚአብሔርና ከመንፈሳዊ ሕይወት ሊያስወጣን የማያደርገው ጥረት የለም። በምንወደው ነገር ይፈትነናል። ይኸም አልሳካ ሲለው በውዳሴ ከንቱ ለመጣል ይፈትነናል። በዚህም ብዙዎችን ከክርስትና ሕይወት አውጥቶ የእርሱ ፈቃድ ፈጻሚዎች አድርጓቸዋል። የመላእክት አለቃ የነበረው ሳጥናኤልን ለመውደቅ ያበቃው ያልተሰጠውን ክብር በመፈለጉ ነው። የተሰጠውን ትቶ ከሚገባው በላይ ታላቅነት ሽቷልና እንዲህ ብሏል "ወደሰማይ አርጋለሁ ዙፋኔንም ከእግዚአብሔር ከዋክብት በላይ ከፍ ከፍ አደርጋለሁ። ከደመናዎች ከፍታ በላይ አርጋለሁ። በልዑልም እመለሳለሁ" (ኢሳ. ፲፬÷፲፫) ሳጥናኤል እንደ እግዘአብሔር ለመሆን ፈለገ ነገር ግን ትዕቢቱ ውርደትን እንጂ ክብርን አላስገኘለትም። አዳምና ሄዋን ትእዛዘ እግዘአብሔርን እንዲጥሱ ያደረጋቸው ከገነት የተባረሩት፣ ጸጋቸው የተገፈፈው ያልተሰጣቸውን ክብር በመፈለጋቸው ነው። ጥንተ ጠላታችን ዲያብሎስ በውዳሴ ከንቱ ጠልፎ በመጣል ነው ለውድቀት የዳረጋቸው።(ዘፍ. ፫÷፭)

በእግዘአብሔር ቤት ያለንና ስአገልግሎት የተሰማራን ሰዎች በምናደርጋቸው መንፈሳዊ ሥራዎች፤ እኛን ለመጥቀምም ሆነ ለመጉዳት በተለያየ መንገድ ከሚገባን በላይ ክብርን ሲለግሱንና ሲቸሩን፤ እንደ ቅዱሳን አባቶቻችን ራሳችንን ዝቅ በማድረግ ጠላታችን ዲያብሎስ ልናሳፍረው ይገባናል። (፩ቆሮ.፲፭÷ ፱፣ መዝ. ፳፩÷፮) ነገር ግን የትህትና ሰዎች ብቻ ለመባል በውስጣችን ክብርን ፈልገን ሳይሆን፤ ከውስጣዊ ስሜት በመነጨ የትህትና አነጋገር"በውጪ አምሬ የምታይ ውስጤ ግን በደለኛ ነኝ፣ ሳይገባኝ ነው በቤቱ ውስጥ ያለሁት፣ እግዚአብሔር ነው በእኔ አድሮ የሰራው።" በማለት ከእኛ ይልቅ የእግዚአብሔር ስም እንዲመሰገን የቅዱሳን ክብር እንዲገለጽ ልናደርግ ይገባል።

ከክርስቲያኖች መካከል አጋንንትን የማራቅ፣ ድውይ የመፈወስ፣ ሙት የማስነሳት፤ ገቢረ ተአምራት ወመንክራት፣ የራዕይና የትንቢት፣ የማስተማርና የመዘመር፣ የአዲስ ድርሰት ጸጋም ቢሆን፣ የረጅም ጊዜ ጾምና ጸሎት፣ ትግሀ ሌሊት፣ ሱባዔ ወዘተ ከአምላክ ቢሰጠውና መንፈሳዊ ኩራት እያለ ሌሎችን በመናቅ ሲኮራና ሲኩራራ ቢኖር፤ ይህ ጸጋው ከሲኦል እስር ቤት ከዲያብሎስና ሠራዊቱ አያድነውም።

ከላይ የተዘረዘሩትን ስጦታዎች በትህትና ካልያዝናቸው ምድራዊውንና ጊዜያዊውን ውዳሴ ከንቱና ክብር ቢያስገኙልን እንጂ፤ ሰማያዊውንና ዘላለማዊውን ክብርና ዋጋ አያስጠንምና ከኩራት ወደ ትህትና እንመለስ። ለሌሎች ሥውር የሆነውን በእግዚአብሔር ፊት ግን የተገለጸውን ድካማችንን ጉድለታችንንና በደላችንን እያስታወስን እንደኛ ሥራ ሳይሆን እንደቸርነቱ ጸጋውን ያላጎደለብንን እግዚአብሔርን እያመሰገንን ሁሉን ለእግዚአብሔር ክብር እንስጥ።